ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ

ኪል-003/07
ጥር 5 ቀን 1999 ዓ. ም.

# እጅ ለእጅ ተያይዞ መቆሚያው ጊዜው ዛሬ ነው

በከባድ ፍጥነት እየተለዋወጠ ባለው የአለማችን ሁኔታ ለመብት መከበር፣ ለነጻነት መረጋገጥና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መስፈን እየተደረገ ያለው ተጋድሎ ከምንጊዜውም በላይ እየተጠናከረ ይገኛል:: አምባገነኖች የዜጎችን ነጻነት በመሳሪያ ሃይል የገደቡ ይምስላቸው እንጂ ፈጽሞ ማቆም አልተቻላቸውም:: ህዝባችንም የዚህ ፈጣን ሂደት አካል በመሆኑ ለነጻነቱ ያለው ቀናኢነትና ተቆርቋሪነት ከምንጊዜውም በላይ እየተጠናከረና መብቱ እንዲከበርለትም እየተዋደቀ ነው:: ባርነትን ተቀብሎ በጸጋ መኖር የማይቻል መሆኑን በግንቦቱ ምርጫ አስመስክሯል ::

እንደ ዘመነ መሳፍንት በጎሳ ከፋፍለው አንድነቱን ሊቦረቡሩት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም:: በወርሃ ግንቦት 1997 ዓ.ም ለረጅም ሰአታት ተሰልፎ የምርጫ ካርዱን የወደፊት ተሰፋዬን ሊያለመለምልኝ ይችላል ብሎ ላመነባቸው ለቅንጅትና ለሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች በመስጠት የስልጣን ምንጭነቱንና ባለቤትነቱን አስመስክሯል። በዴሞክራሲ ስም እየማሉና እየተገዘቱ አለም አቀፉን ህብረተሰብ ሲያታልሉ የነበሩ የወያኔ/ኢህአዴግ ገዥዎች ለለውጥ ያልተዘጋጁ መሆናቸውን በገሃድ ያሳወቁበት ሁኔታ እንዲፈጠር አሸችሏል። የኢትዮጵያ ህዝብ በመራራ ትግሉና በአኩሪ መስዋእትነቱ ለመብቱና ለነጻነቱ በተከታታይ አምባገነኖችን እየተፋለመ በደሙ ታሪካዊ ገድል እየጻፈ ይገኛል :: የወያኔ/ኢህአዴግ አምባገነኖች በድምጹ የመረጣቸውን መሪዎቹን በመግደልና በማሰር በሚወስዱት ግፈኛ እርምጃ የነጻነቱን ትግል ግለት መቀነስ ፈጽሞ አልተቻላቸውም።

ውድ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ መሪዎቹም ትናንት በማኒፌስቶው ለኢትዮጵያ ህዝብ የገቡለትን ቃል ኪዳን በማፍረስ ለወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ወከባ በመንበርከክ አላሳፈሩትም። የህዝብ ጆሮና አይን ሆነው የማወቅ መብቱን ለማስከበር ደፋ ቀና ይሉ የነበሩ የነጻው ፕሬስ ህብረተሰብ አባላትም ላገዛዙ አልተንበረከኩም። የዴሞክራሲ ስርአት መሰረት የሆኑት የሲቪክ ህብረተሰብ አባላት መሪዎችም ለህይወታቸው ሳይሳሱ ለህጋዊነት ከመታገል ወደ ኋላ አላሉም። የህብረተሰባችን ትኩስ ሃይል የሆነውና የነገው ትውልድ ገንቢና ተረካቢ በታላቅ ወገናዊ ፍቅር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ሲል በአገር በቀል ጨካኞች ጥይትና ሣንጃ ክቡር ህይወቱን ገብሯል፣ ደሙን አፍስሷል፣ በግፈኞች ተግዟል፣ ዛሬም እየተጋዘ ይገኛል።

ይህ ኢትዮጵያን ወደ ዜጎች እስር ቤትነት የለወጠው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በህዝብ የተመረጡ መሪዎችን አስሮና ገድሎ ዛሬም ያገዛዝ ዘመኑን በመሳሪያ ሀይል ለመቀጠል ወስኖ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህ አገዛዝ የህዝባችንን ፍቃድ ረግጦ በግፍ ያሰራቸውን መሪዎቻችንን እንዲፈታና ወደ ብሄራዊ እርቅ እንዲመጣ የቀረበለትን አገራዊና አለም አቀፍ ጥሪ ወደ ጎን በመተው የሀሰት ክስ መስርቶ በተፈበረከ መረጃና የሀሰት ምስክር፣ የፖለቲካ ታማኝ ካድሬ ዳኞቹን በመመደብ በፍትህና

*በዳኝነት ላይ በመቀለድ ላይ ይገኛል። ይህ ባገዛዙ የተጀመረው የዳኝነት ቲያትር በየካቲት ወር በንፁኃን መሪዎቻችንና ወገኖቻችን ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በመስጠት ለመደምደም ይሞከራል የሚለው ስጋት አለ። ይህንን በህግ ስም እየተካሄደ ያለ ያገዛዙን ህገ ወጥ ተግባር ህብረተሰቡ ለመከላከል እንዳይችል በጎን ማዋከብና እስራቱን በሰፊው በመቀጠል በሌላ ወገን በተለመደው የማታልል ስልት የእርቅ ድርድር እየተካሄደ ነው ፣ በቅርቡ ይፈታሉ በሚል ያልተጨበጠ አሉባልታና ተራ ምሬ ስልታዊ ማዘናጊያ እየተካሄደ ይገኛል።*

*በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ አደራዳሪነት ተጀምሮ የነበረውም ድርድር ባገዛዙ ቁንጮዎች ገታራነት የትም ፈቀቅ ሊል አልቻለም። የሰኔና የጥቅምቱ እልቂቶች ፈታውራሪ በረከት ስምዖንም ከአንዳንድ የቅንጂት አመራር አባላት ጋር ያካሄዷቸው ድርድር ተብየዎችም ካለምንም ምክንያትና ውጤት ተቋርጠዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ያልተዘጋጀና ለህዝብ ፈቃድ እራሱን ለማስገዛት ፈቃደኛ አለመሆኑን በግልጽ የሚጠቁሙ መረጃዎች ናቸው።*

*ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው ታሪካዊ አማራጭ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የጀመረውን ሰላማዊ ትግል አጠናክሮ መቀጠል ብቻ ነው። ይህ ሰለማዊ ትግል በአገር ውሥጥና በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት <u>"የሃሰት ክስ ያብቃ፣ ቅንጅት መሪዎችና ሌሎችም የህሊና እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ፣ ብሄራዊ የእርቅና የሰላም ጉባዔ በአስኳይ ይደረግ "</u> በሚል መሪ መፈክር ስር የሚካሄድ የተቀነባበረ አለም አቀፍ ባለ ብዙ ዘረፍ እንቅስቃሴ ይደረጋል። በዚህ ከፍተኛ ብሄራዊና አለም አቀፋዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ አማካይነት ወያኔ በግፍ አስሮ ሃሰት ክስ መስርቶ የሚያንገላታቸውን የቅንጅት መሪዎችን፣ጋዜጠኞችንና ሲቪክ ማህበራት ተወካዮችን ከየካቲት 12. 1999 የፍርድ ብያኔ በፊት እንዲፈቱ ወይም በእብሪት ወንጀለኛ የሚደርጋቸውን ፍርድ ማስተላለፍ እዳይችል ማድረግ ነው።*

*ይህ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መሪዎቻችንን በማስፈታት የሚያበቃ ብቻ ሳይሆን በአገራችን እንዲገነባ የታገልንለትና አኩሪ መስዋዕትነት የከፈልንበት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት እውን እስኪሆን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ይህንን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ለማድረግ በአገርም ውስጥ ሆነ በወጭ አገር የምንገኝ የህዝብ ወገኖች በፖለቲካ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ሳንከፋፈል እጅ ለእጅ ተያይዘን መነሳት ይኖርብናል። የወያኔ አገዛዝ የፈጠራ ክሱን ሰርዞ የታሰሩ የህዝብ ልጆችንና መሪዎቻችን ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈቶ ለህዝባችን ፈቃድና ለህግ እራሱን እስከሚያስገዛ ድረስ ተባብረን እንድንታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን !*

***የተባበረ ህዝብ ምንጊዜም አሸናፊ ነው !***

## ***የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ***

**Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701- Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-206-3974 www.kinijitethiopia.org**